መልእክት አራት

## የሕይወት ዛፍ ክፍል ለመሆን ከክርስቶስ ጋር በተጋቦ መጋጠም

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዘፍ. 2፡9፤ 1 ቆሮ. 6፡17፤ ሮሜ 11፡17፣24፤ ዮሐ. 15፡1፣ 4-5

**I. እግዚአብሔር ከሰው ጋር እንዲኖረው የሚፈልገው ግንኙነት እርሱና ሰው አንድ ይሆኑ ዘንድ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልገጣል—1 ቆሮ. 6፡17፦**

ሀ. ወደ መጽሐፍ ቅዱስ በመጣን ጊዜ ሁሉ አንድ መርህ መጠቀም አለብን—እግዚአብሔር ከመረጣቸው ሕዝቡ ጋር አንድ መሆን የመፈለጉን መርህ—ዮሐ. 14፡20።

ለ. የእግዚአብሔር ዋና ዓላማ ራሱን ከሰው ጋር አንድ ማድረግ እና ሰውን ከራሱ ጋር አንድ ማድረግ ነው—ኤፌ. 4፡4-6።

ሐ. እግዚአብሔር መለኮታዊው ሕይወት እና የሰብዕና ሕይወት አንድ ሕይወት ይሆኑ ዘንድ እንዲጋጠሙ ይፈልጋል።

መ. የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ማዕከላዊው መስመር ሁለቱ በአንድ ሕይወት እና በአንድ ባሕሪ አንድ ኑሮ ይኖራቸው ዘንድ፣ እግዚአብሔርን እና ሰውን፣ ሰውን እና እግዚአብሔርን አንድ አካል ማድረግ ነው—ራእ. 22፡17።

ሠ. በተሠግዎው ክርስቶስ እግዚአብሔርን ወደ ሰው ውስጥ አመጣው፣ በትንሣኤው ሰውን ወደ እግዚአብሔር ውስጥ አመጣው፤ በዚህ የእግዚአብሔርን እና የሰውን እንደ አንድ መዋሐድን አከናወነ—ሮሜ 8፡3፤ 1፡3-4፦

1. እኛ በክርስቶስ ውስጥ ነን፣ እርሱ በእኛ ውስጥ ነው፤ እርሱ እና እኛ አንድ ማንነት ሆነናል—1 ቆሮ. 12፡12።
2. ክርስቶስ እኛን ሆነ፣ እኛም እርሱን ሆንን—ዕብ. 2፡14፣ 11።

**II. እግዚአብሔር ከሰው ጋር እንዲኖረው የሚፈልገው ግንኙነት እርሱ እና ሰው አንድ ላይ በተጋቦ ይጋጠሙ ዘንድ እና ከዚህ የተነሣ በሕይወታዊ ጥምረት ውስጥ አንድ ይሆኑ ዘንድ ነው—ሮሜ 6፡3-5፤ ዮሐ. 15፡4-5፦**

ሀ. በተጋቦ የተጋጠመ ሕይወት አንዱ ሕይወት በሌላው የተተካበት ሕይወት አይደለም—የሰው ሕይወት ከመለኮታዊው ሕይወት ጋር መዋሐድ ነው—1 ቆሮ. 6፡17።

ለ. በተጋቦ መጋጠም፣ ሁለት ተመሳሳይ ሕይወቶች ይጣመራሉ፣ ከዚያም ሕይወታዊ በሆነ መንገድ አብረው ያድጋሉ—ሮሜ 11፡24፦

1. የሰው ሕይወታችን በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ስለተሠራ ከመለኮታዊው ሕይወት ጋር መጋጠም ይችላል—ዘፍ. 1፡26።
2. የሰብዕና ሕይወታችን ከመለኮታዊው ሕይወት ጋር ይመሳሰላል፤ ስለዚህ መለኮታዊው ሕይወት እና የሰብዕና ሕይወት አብረው በተጋቦ መጋጠም እና አብረው መኖር ይችላሉ።

ሐ. ወደ ክርስቶስ ውስጥ በተጋቦ ለመጋጠም፣ ሕይወት-የሚሰጥ መንፈስ ይሆን ዘንድ እርሱ በተሠግዎ፣ በስቅለት እና በትንሣኤ ሂደቶች ውስጥ ማለፍ ነበረበት—ዮሐ. 1፡14፤ 1 ቆሮ. 2፡2፤ 15፡45።

መ. የሕይወት ዛፍ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ ውስጥ በተጋቦ ተጋጥመናል፣ ይህም በተጋቦ መጋጠም ከእርሱ ጋር አንድ አድርጎናል—ሮሜ 11፡24፦

1. ክርስቶስ እና አማኞቹ አንድ ዛፍ ናቸው፤ እርሱ የወይኑ ተክል ነው፣ እኛም ቅርንጫፎች ነን—ዮሐ. 15፡1፣ 5፣ 4።
2. ክርስቶስ ሕይወታችን፣ ባሕሪያችን እና ማንነታችን ሆኗል—ቆላ. 3፡4፣ 10-11፤ ኤፌ. 3፡17።

ሠ. ወደ ክርስቶስ ውስጥ በተጋቦ እንደተጋጠሙ ዳግም እንደተወለዱ ሰዎች በተጋቦ የተጋጠመ ሕይወት፣ ሁለት ወገኖች ሕይወታዊ በሆነ መንገድ ለማደግ የተጋጠሙበትን ሕይወት መኖር አለብን፦

1. ወደ ክርስቶስ ውስጥ በተጋቦ ስለተጋጠምን በራሳችን መኖር የለብንም፤ ይልቁንም እስትንፋሳዊው ክርስቶስ በውስጣችን ይኖር ዘንድ መፍቀድ አለብን—ገላ. 2፡20።
2. በሥጋችን ወይም በተፈጥሮአዊ ማንነታችን መኖር የለብንም፤ ይልቁንም በተዋሐደው መንፈስ—ዳግም ከተወለደው መንፈስ ጋር በተዋሐደው መለኮታዊ መንፈስ—የተጋጠመ ሕይወት መኖር አለብን—1 ቆሮ. 6፡17፤ ሮሜ 8፡4።

ረ. በተጋቦ በተጋጠመው ሕይወት የሰብዕና ሕይወት አይወገድም፣ ነገር ግን በመለኮታዊው ሕይወት ይጠነክራል፣ ከፍ ይደረጋል፣ ይበለጥጋል—ገላ. 2፡20፤ 4፡19፤ ኤፌ. 3፡16-17፦

1. በተጋቦ በተጋጠመው ሕይወት ቅርንጫፉ [ከግንዱ ጋር] የሚመሳሰሉትን የራሱን አስፈላጊ ባሕሪያት ይጠብቃል፣ ነገር ግን ከፍ ካለ ሕይወት ጋርም በመጋጠም ይጠነክራል፣ ከፍ ይደረጋል፣ ይለወጣል—ዮሐ. 15፡4-5፤ ሮሜ 11፡17።

2. በተጋቦ በተጋጠመው ሕይወት መለኮታዊው ሕይወት አሉታዊ ነገሮችን ለማስወገድ በውስጣችን ይሠራል፡-

*ሀ. ተፈጥሮአዊ የሆነውን ነገር ሁሉ ለማስወገድ መለኮታዊው ሕይወት ቀስ ባለ መንገድ ይሠራል።*

*ለ. መለኮታዊው ሕይወት እንከኖቻችንን እና ድካሞቻችንን ይውጣል።*

*ሐ. የግል ባሕሪያችን አሉታዊ ንጥረ-ነገር ይገደላል፣ ከዚያም ጌታ፣ ባሕሪያችንን ከማስወገድ ይልቅ ከፍ ያደርገዋል፣ ይጠቀምበታልም።*

3. በተጋቦ በተጋጠመው ሕይወት መለኮታዊው ሕይወት የእግዚአብሔርን የመጀመሪያ ፍጥረት በትንሣኤ ያስነሣዋል፣ ሥነ-ልቦናዊ አቅሞቻችንንም ከፍ ያደርጋል—ዮሐ. 11፡25፤ ኤፌ. 4፡23፡-

*ሀ. መለኮታዊው ሕይወት አሉታዊ ነገሮችን ሲያስወግድ ሳለ፣ የእግዚአብሔርን የመጀመሪያ ፍጥረት በትንሣኤ ለማስነሣት ይሠራል።*

*ለ. በዚህ መንገድ የመጀመሪያ አገልግሎቶቻችን—ስንፈጠር ያገኘናቸው አገልግሎቶቻችን—ይመለሳሉ፣ ይጠነከራሉ፣ ከፍም ይደረጋሉ—ገላ. 2፡20።*

4. በተጋቦ በተጋጠመው ሕይወት መለኮታዊው ሕይወት ወደ ውስጣዊው ክፍሎቻችን የክርስቶስን ብልጥግናዎች እንደ አቅርቦት ይሰጣል፣ መላው ማንነታችንንም ይሞላዋል—ሮሜ 12፡2፤ 8፡29-30።

**III. እንደ ሕይወት ዛፍ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አካል መልበስ ነው፣ ከክርስቶስ ጋር በመጋጠማችንም ከእርሱ ጋር ሕይወታዊ በሆነ መልኩ ከእርሱ ጋር ተጣምረናል፣ ከዚህም የተነሣ የሕይወት ዛፍ ክፍል ነን—ቆላ. 2፡9፤ ዮሐ. 15፡1፣ 4-5፡-**

ሀ. ክርስቶስን እንደ ሕይወት ዛፍ የምንመገብ ብቻ ሳንሆን—ከእርሱ ጋር ተጣምረናል፣ የእርሱም ክፍል ነን—1 ቆሮ. 6፡17።

ለ. የሕይወት ዛፍ መለኮታዊውን ሕይወት ወደ ውስጣችን ለማደል ነው፤ እኛ ቅርንጫፎች፣ በወይን ተክሉ ውስጥ ስንኖር ሳለ ከሕይወት ዛፉ የሕይወትን እደላ እንቀበላለን፣ እንደ ሕይወት ዛፉ ክፍልም እንኖራለን—ዮሐ. 15፡5፤ ሮሜ 8፡2፣ 10፣ 6፣ 11፤ ተዛ. ፊልጵ. 4፡13።

ሐ. ራሱን ወደ ውስጣችን ያድል ዘንድ እንደ የሕይወት ዛፍ ክርስቶስ ለመለኮታዊው ኢኮኖሚ ነው፤ እንደ የወይን ተክሉ ቅርንጫፎች በእርሱ ውስጥ እየኖርን ነው፣ እርሱም በእኛ ውስጥ እየኖረ ነው።

መ. በወይን ተክሉ ውስጥ ስንኖር፣ ወደ ውስጣችን የእግዚአብሔር እደላ፣ ከሕይወት ዛፍ ወደ ቅርንጫፎቹ ውስጥ የሕይወት እደላ አለ፤ ይህ እደላ እኛን አምላክ-ሰዎች ያደርገናል—ሮሜ 8፡10፣ 6፤ 11።

ሠ. እንደ የወይን ተክሉ በክርስቶስ ውስጥ መኖር እርሱን እንደ መኖሪያ ስፍራችን መውሰድ ነው፣ ይህም እጅግ ከፍተኛው እና እጅግ ሙሉ የሆነው የእግዚአብሔር ልምምድ ነው፤ በክርስቶስ ውስጥ መኖር ኑሯችን በክርስቶስ ውስጥ መሆኑ፣ እርሱን እንደ ሁሉ ነገራችን መውሰዳችን ነው—መዝ. 90፡1፤ 91፡1፣ 9።

ረ. እንደ የሕይወት ዛፍ ክፍል የምንኖር ከሆነ ግድ የምንሰኘው ለመልካም ወይም ለክፉ ሳይሆን ለሕይወት ነው፣ ነገሮችንም የምንለየው ትክክል ወይም ስህተት ከመሆናቸው አኳያ ሳይሆን ከሕይወት ወይም ከሞት አኳያ ነው—ዘፍ. 2፡9፣ 16-17፤ 2 ቆሮ. 11፡3።

*© 2022 Living Stream Ministry*